የወ/መ/ቁጥር 164081

የልደታ ምድብ 5 ኛ ወንጀል ችሎት

ሐምሌ 07 ቀን 2002 ዓ.ም

ዳኛ ውበቱ አሰፋ

ከሳሽ፡ የፌደራል ዐ/ሕግ - አቶ መሳይ ተድላ ቀረበ

ተከሳሽ፡ 1 ኛ አቶ ወልዴ አደም ባኮ - ቀረቡ

2 ኛ አቶ ተስፋዬ መኮንን አሊ - ቀረቡ

መዝገቡ ተመርምሮ የሚከተለው ፍርድ ተሰጠ።

<u>ፍርድ</u>

ዐ/ሕግ ታህሳስ 05 ቀን 2002 ዓ.ም በተፃፈ የወንጀል ክስ አቤቱታ በአንደኛው ክስ አንደኛ ተከሳሽ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በሌላ ሰው ላይ ፍርሀትን በሚቀሰቅስ ሁኔታ ጥቅምት 16 ቀን 2002 ዓ.ም በግምት ከምሽቱ 1፡30 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 ልዩ ቦታው ድል ጮራ አካባቢ ግል ተበዳይ አቶ ንጉሴ በላይን ካቻ ቢቴ በመያዝ እስራልሀሉ፤ አስተነፍስሀለሁ ብሎ በማስፈራራቱ በፈፀመው የዛቻ ወንጀል፤ ሁለተኛ ተከሳሽ ደግሞ በሁለተኛው ክስ በ1996 ዓ.ም የወጣውን የወንጀል ሕግ አንቀፅ 560(1) ላይ የተደነገገውን በመተላለፍ በሰው አካልና ጤና ላይ ጉዳት ሳያደርስ በአንደኛው ክስ በተጠቀሰው ቀን፤ ሰዓትና ቦታ የግል ተበዳይ አቶ ንጉሴ በላይን ልብስ ይዞ በመጎተት በፈፀመው የእጅ እልፊት ወንጀል ተከሰዋል በማለት ያቀረበ ሲሆን የዐ/ሕግ የክስ አቤቱታ ለተከሳሾች ደርሷቸውና ተነቦላቸው ከተረዱት በኋላ ክሱን ሳይቃወሙ፤ ድርጊቱን አልፈፀምንም፤ ጥፋተኞችም አይደለንም ብለው ክደው በመከራከራቸው ዐ/ሕግ የግል ተበዳይን ጨምሮ ሦስት ምስክሮችን በማቅረብ ያሰማ ሲሆን የተሰሙት ምስክሮችም ጥቅምት 16 ቀን 2002 ዓ.ም ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት ሲሆን በኮልፌ ቀራንዮ ክፍለ ከተማ ቀበሌ 06 ምዕራብ ጮራ ዕድር ቤት ግቢ ውስጥ አንደኛ ተከሳሽ አቶ ወልዴ ከአቶ ንጉሴ ጋር ተጣልተው ንጉሴን እሰራልሀለሁ ሲል ሰምተናል ብለው መስክረዋል፤ ካቻቢቴም በእጁ ይዞ የነበረ መሆኑን አስረድተዋል። ሁለተኛ ተከሳሽን በሚመለከት ሁለተኛው ምስክር እና ሦስተኛው ምስክር የግል ተበዳይን ይዞ ጎትቶታል ሲሉ መስክረዋል። ስለዚህ ተከሳሾች እንዲከላከሉ በማለት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 142(1) መሰረት ታዘዋል።

ተከሳሾችም እንከላከላለን ብለው ሦስት የመከላከያ ምስክሮችን በጋራ አቅርበው ያሰሙ ሲሆን በጭብጥነትም በዕለቱ ከምሽቱ 12፡30 ሰዓት ሲሆን ተከሳሾች ለቁጥጥር ስራ ወደ ዕድሩ ቤት

ስንገባ ሁለት ጥበቃዎች/ዛሬ በመከላከያ የቀረቡት/ ብቻ እንጅ የአሁን የግል ተበዳይ አልነበረም፤ እኛም የዕለት ስራችን በመስራት ላይ እያለን ከምሽቱ 1፡00 ሰዓት ሲሆን የግል ተበዳይ ወደ ጥበቃ ቦታው ስላልመጣ በመዝገቡ ላይ ቀሪ የተባለ ሲሆን፤ ከዚያ በኋላ ሲመጣ ትንሽ መጠጥ ቀማምሶ ስለነበር ረብሻ ጀመረ፤ እኛንም መሳደብ ጀመረ፤ ሊደበድብ ሲል በኋላ የፖሊስ አባል ጠርተን ነገሩ እንዲበርድ አድርገናል፤ በዚህ ጊዜ ሁለቱ የጥበቃ አባለት ስለነበሩ እኛ ምንም እንዳላደረግን እናስረዳልን በማለት አስመዝግበው የመከላከያ ምስክሮቹም ቀርበው በእምነታቸው መሰረት መኃላ ፈፅመው የመሰከሩ ሲሆን ቃላቸውም ከመዝገቡ ጋር ተያይዞ ይገኛል።

ፍ/ቤቱም ተከሳሽ ባቀረበው የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበበትን ክስና ማስረጃ አስተባብለዋል ወይ የሚለውን ነጥብ የመረመረ ሲሆን የተከሳሾች ሁለት የመከላከያ ምስክሮች ማለት የጥበቃ አባላት እንዳስረዱት በዕለቱ ተከሳሾች አዳራሽ ውስጥ እያሉ የግል ተበዳይ ወደ እነሱ አሉበት ቦታ ደርሰው ጭቅጭቅ ሲያደርጉ ነበር፤ በዚህ ጊዜ ምን እንደተፈፀመ አላየንም፤ ምክንያቱም እኛ በር ላይ እየጠበቅን ነበር ስላሉ በዕለቱ አንደኛ ተከሳሽ የዛቻ የወንጀል ድርጊት ይፈፅሙ ወይም አይፈፅሙ በግልፅ ያላስረዱ ሲሆን፤ ሁለተኛ ተከሳሽንም በተመለከተ እንዲሁ በተመሳሳይ ሁኔታ አዳራሽ ውስጥ የተፈፀመውን ያላስረዱ ስለሆነ፤ እንዲሁም ሦስተኛው የመከላከያ ምስክርም ፀቡ ከተፈጠረ በኋላ ዘግይተው የመጡ ስለሆነ ተከሳሾች የተከሰሱበትን ድርጊት አልፈፀሙም ብሎ ለማሰረዳት የሚችል አይደለም። በመሆኑም በአጠቃላይ ተከሳሾች ባቀረቡት የመከላከያ ማስረጃ በዐ/ሕግ በኩል የቀረበባቸውን ክስና ማስረጃ ያላስተባበሉ ስለሆነ፤ አንደኛ ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 580 ስር፤ ሁለተኛ ተከሳሽ በወንጀል ሕግ አንቀፅ 560(1) ስር ጥፋተኛ ናቸው በማለት በወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ሥነ ሥርዓት ቁጥር 149(1) መሰረት ውሳኔ ተሰጥቷል።

<u>የቅጣት አስተያየት</u>

<u>ዐ/ሕግ</u>፡ የቅጣት ማክበጃና ማቅለያ የለንም፤ አንደኛ ተከሳሽ የዛቻ ድርጊቱን ሲፈፅሙ መሳሪያው ከባድ ባለመሆኑ ፍ/ቤቱ የወንጀሉን ደረጃ መካከለኛ ብሎ ቢወስን በማለት አመለከተ።

<u>ተከሳሽ</u>፡ 1 ኛ ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 42 ዓመት ነው፤ ሥራዬ የግል ንግድ ነው፤ የወር ገቢዬ ይህ ነው የሚባል አይደለም ምክንያቱም ተባባሪ ሥራ ስለምሰራ ነው፤ አራት ልጆች አሉኝ፤ የትምህርት ደረጃዬ 12 ኛ ክፍል ነው በማለት አመለከቱ

2 ኛ ተከሳሽ፡ ዕድሜዬ 59 ዓመት ነው፤ ሥራ የለኝም፤ በአሁኑ ውቅት ጡረተኛ ነኝ በወር ብር 300.00(ሦስት መቶ ብር) አገኛለሁ፤ ትዳር አለኝ፤ አምስት ልጆች አሉኝ፤ የትምህርት ደረጃዬ 10 ኛ ክፍል ነው

በማለት አመለከቱ።

ፍ/ቤቱ ጉዳዩን መርምሮ የሚከተለውን ቅጣት ወስኗል።

<u>ውሳኔ</u>

በወንጀል አድራጊ ላይ የሚወሰነው ቅጣት ወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ በሚያሳካ መልኩ ሊሆን እንደሚገባ የታመነ ነው። በዚህም መሰረት የወንጀል ሕግ ዓላማ ለጠቅላላው ጥቅም ሲባል የአገሪቱን መንግስት፤ የነዋሪዎቿን ሰላም፤ ደህንነት፤ ሥርዓት፤ መብትና ጥቅም መጠበቅና ማረጋገጥ ነው።

የወንጀል ሕግ ግብ ደግሞ በዋናነት ስለወንጀሎችና ስለቅጣታቸው በቅድሚያ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ወንጀል እንዳይፈፀም መከላከል ሲሆን፤ ሕጉን ተላልፈው ወንጀል የሚፈፅሙትን ደግሞ ተቀጥተው ሌሎች ወንጀል እንዳይፈፅሙ፤ እንዲቆጠቡና ለሌሎች ማስተማሪያ እንዲሆኑ ወይም እንዲታረሙ በማድረግ ወይም ተጨማሪ ወንጀሎች እንዳይፈፀሙ እርምጃዎች እንዲወሰድባቸው ማድረግ ስለመሆኑ በ1996 ዓ.ም ከወጣው የኢ.ፌ.ዲ.ሪ.የወንጀል ሕግ አንቀፅ 1 ድንጋጌ ለመገንዘብ ይቻላል።

የወንጀል ሕጉን ግብና ዓላማ ለማሳካት ፍ/ቤቱ በወንጀለኛው ላይ የሚወስነው ቅጣት በአንድ በኩል ወጥነትን፤ ተመዛዛኝነትን እና ፍትሀዊነትን ለማረጋገጥ በሌላ በኩል ደግሞ የወንጀል አድራጊውን ግላዊ ባህሪና የወንጀል አፈፃፀም ኩበደት መዝኖ ቅጣት ለመወሰን እንዲያስችል ታስቦ የወጣውን የፌደራል ጠቅላይ ፍ/ቤት የወንጀል ቅጣት አወሳሰን መመሪያ ቁጥር 1/2002 እና የወንጀል ሕጉን ድንጋጌዎች መሰረት ተደርጎ የሚከተለው ቅጣት ተወስኗል።

አንደኛ ተከሳሽ አሁን ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 580/የዛቻ ወንጀል ገና ደረጃ ያልወጣለት በመሆኑ የወንጀል ደረጃ እና እርከን የሚወሰነው በቅጣት አወሳሰን መመሪያው አንቀፅ 13 መሰረት ነው። የደረጃ አወሳሰኑም ማክበጃውና ማቅለያው ታሳቢ ከመደረጉ በፊት በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት እንደሚወሰን መመሪያው በደነገገው መሰረት ደረጃው በሦስት ደረጃዎች ሀ. ዝቅተኛ፤ ለ. መካከለኛ እና ሐ. ከባድ ደረጃ በማለት ይለያል።

ፍ/ቤቱም በወንጀሉ ክብደትና አፈፃፀም መሰረት ወንጀሉ የተፈፀመው በምሽት ቢሆንም በወቅቱ ከግል ተበዳይና ከተከሳሹ ጋር ሌሎች ሰዎች ስለነበሩ፤ ከባድና ገዳይ የሆነ መሳሪያ በመያዝም ያልተፈፀመ በመሆኑ የወንጀል ደረጃው ዝቅተኛ ነው ተብሎ ተወስኗል።

በወጣው ደረጃ መሰረት እርከን ለመወሰን በሕጉ አንቀፅ 580 ለወንጀሉ የተቀመጠው ከአምስት መቶ ብር በማይበልጥ መቀጮ ወይም ከስድስት ወር በማይበልጥ ቀላል እስራት ስለሆነ፤ ከተፈፀመው የወንጀል ድርጊት አንፃር ተከሳሹን የሚያርመው በገንዘብ መቀጮ ቢቀጣ መሆኑን ፍ/ቤቱ ስለተረዳ፤ ዝቅተኛ የሚለውን ደረጃ የሚለው የሚወድቀው ከአስር ብር እስከ አንድ መቶ

ስላስ ስድስት ብር ባለው መካከል ስለሆነ በመመሪያው አንቀፅ 13(10) መሰረት ከተከሳ ሽ ገቢ አንፃር በብር 160.00(አንድ መቶ ስልሳ ብር) መቀጮ እንዲቀጣ ተወስኗል።

ሁለተኛ ተከሳሽ ጥፋተኛ የተባለበት በ1996 ዓ.ም የወጣው የወንጀል ሕግ አንቀፅ 560(1) ደረጃ የወጣለት ወንጀል በመሆኑ በቅጣት አወሳሰን መመሪያው ክፍል ሦስት ንዑስ ክፍል አንድ እና አባሪ 3 መሰረት የተመለከተው ደረጃ 1 ሲሆን ተጓዳኝ መነሻ እርከኑም የእስራቱ 2 ሲሆን የገንዘብ ከሆነ ደግሞ እርከኑ 1 ነው። ፍ/ቤቱ ሁለተኛ ተከሳሽ ከፈፀመው የወንጀል ደርጊት አንፃር በገንዘብ መቀጮ እንዲቀጣ ወስኗል። በዚህም መሰረት የዚህ እርከን 1 መነሻ ፈቃደ ስልጣን/range/ ከብር አስራ እስከ ብር አንድ ሺህ ስለመሆኑ የመመሪያው አባሪ 2 ይገልፃል። በመሆኑም ፍ/ቤቱ ቅጣቱን የሚወስነው የተከሳሽን የትምህርት ደረጃ፤ የገቢ ምንጭ እና ዕድሜ ከግምት ውስጥ በማስገባት ሆኖ በብር 200.00(ሁለት መቶ ብር) መቀጮ እንዲቀጡ ተወስኗል።

<u>ትዕዛዝ</u>

1 ኛ. ተከሳሾች የተወሰነባቸውን የቅጣት ገንዘብ ሲከፍሉ ይለቀቁ።

2 ኛ. የይግባኝ መብት እንዳለ በችሎት ተነገረ።

3 ኛ. በዚህ መዝገብ የተገባ የዋስትና ግዴታ ቀሪ ሆኗል።

4 ኛ. መዝገቡ ተዘጋ ወደ መዝገብ ቤት ይመለስ።